ህልም እንዲሆን አምላኬን ተማጸንኩት
ቅዠት ነው ብየ ተሞአገትኩት
ግና ልቤ ፈራ አልሆነም
እናንዬ ጉድሽ ፈላ
ብሪ አነደበትህ ተዘጋ
በመከራው ዘመን ያልፈራችሁ
ዛሬ በልጃችሁ ምርር ብላችሁ አነባችሁ
ገልዩ ጋሻሽ ተመታ
ምእራፍ ጠባቂነትሽ ተቀማ
አይ ጉዱ መጣ ደግሞ አመትበአሉ
ምኑ ቅጡ ሲተከ ሳምንቱ
ስጦታው ማቲዬን ማጣቱ
በሉ እመብርሀን ታማልዳችሁ
ፈጣሪአችሁ ያበርታችሁ
እናንየ ሊከሱሽ ነው ወንበሮቹ
ተቀማጩ ሲጎልባቸወ
መጽሀፍቶቹ ሊሞግቱሽ ነው
አንባቢአቸው ሲጠፋባቸው
ቦርሳውም ኡኡ ሊል ነው
አንጋቹ ሲጠፋበት
ብሬ አታውቅም ነበር ምርኮ እስከዛሬ
ዛሬ ግን እጅህን ሰጠህ
ተስፋህ ኩራትህ ተቀማብህ
እንደልጅነትህ አትሽፍት
ልጅህን ልትመልሰው
ከማትችለው ከማትመልሰው
እሩቅ አገር ሄደብህ
አስቱ ተጎድተሻል
በሴቶቹ መሀል አንድ ብርቅ ቢኖርሽ
እብስ ጭልጥ ብሎብሻል
አምላክ በጥበቡ ብልሀቱን ይስጥሽ
ሶስናን ያበርታት ቤተማሬያምን ማሪያም ትታደጋት
ለሜላት ጉልበቱን ፈጣሬ ያልብሳት
የሰራዊት አምላክ
ያችን ሰራዊትን ብርታት ይሸልማት
አስፌ አጎትነትክን ተቀማህ
መድሀኒትአለም ያጠናክርህ
ጌትየ አንጀትህ ተቆርጧል
ያ ትልቁ ጌታ ጽናቱን ያልብስህ
ብሬ እግዚአብሔር ጥናቱን ይስጥህ
እናንየ አምላክ ዘዴውን ችሎታውን ያከናንብሽ
እናም ማትዬ ነበርክ ማለቱን ብንጠላውም
እውነት ሆኖብን ተጨነቅን ተጠበብን
ደህና ሁን የኛ ብላቴና መንገዱ ይለስልስልህ
ጌታችን ከመላክት ጋር ያስቀምጥህ።

**ከደመላሽ ደበበ 12/20/2010**